የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ
ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 196228

ግንቦት 25 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች- አቶ ደምሴ ኦዳ

ተጠሪ- አቶ አሰፋ ወርቁ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ከፍርድ ቤት ውጪ በአማራጭ የሙግት መፍቻ መንገዶች እልባት የተሰጠዉ አንድ የፍትሐብሔር ጉዳይ የፍርድ ደረጃ ተሰጥቶት በቀጥታ ለአፈፃፀም ሊቀርብ የሚችልበትን ሁኔታ የሚመለከት ነዉ፡፡

ጉዳዩ የተጀመረዉም በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ባቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር በቀን 17/03/2010 ዓ.ም ባደረግነው የእርቅ ውል ስምምነት ተጠሪው የአመልካች ይዞታ በሆነው 400 ካ.ሜ ቦታ ላይ ከሰራው ቤት እና አጥር ላይ በ200 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ያለውን አጥር እስከ ቀን 30/05/2010 ዓ.ም ድረስ ለማፍረስ ግዴታ የገባ ቢሆንም በስምምነቱ መሠረት አጥሩን አፍርሶ ይዞታዉን አልለቀቀም፤ በመሆኑም በውሉ መሠረት እንዲያፈርስ እና በስምምነቱ ላይ የተቀመጠዉን ብር 40,000.00 መቀጮ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት የጠየቁትን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ ተጠሪ በሰጡት መልስ አመልካች በክሳቸው ላይ በገለጹት አግባብ ተስማምተናል፤ ሆኖም በስምምነቱ መሠረት የአፈፃፀም ክስ እንጂ መደበኛ ክስ ሊቀርብብኝ አይገባም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ በስምምነታችን መሠረት በ200 ካ.ሜ መሬቱ ላይ ሰርቼ የነበረውን አጥር ስላፈረስኩ መቀጮ ለመክፈል አልገደድም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የተጠሪን መቃወሚያ ውድቅ ያደረገው ሲሆን ፍሬ ነገሩን በሚመለከት ደግሞ ተጠሪ በቦታው ላይ የሰራውን አጥር ለማፍረስ በተስማማው ጊዜ ውስጥ ያላፈረሰ መሆኑን፤ ማፍረስ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ቀን 30/4/13
Federal Supreme Court
Federal Democratic Republic of Ethiopia

የጀመረውም በቀን 29/02/2012 ዓ.ም እንደሆነ፤ ይህም በውል ለማፍረስ ግዴታ ከገባበት ጊዜ በኋላ መሆኑን በመግለጽ መቀጮውን ብር 40,000.00 እንዲከፍል እና በመሬቱ ላይ ያለው ንብረት አንስቶ እንዲለቅ ሲል ወስኗል። በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኙት ተጠሪ ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተሠርዞባቸዋል። በመቀጠል የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅለይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም በአቤቱታው ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ግራ ቀኙ ጉዳያቸውን በእርቅ ስላጠናቀቁ በውሉ መሠረት እንዲፈፀምለት የሚጠይቅ ወገን የአፈፃፀም ክስ ከማቅረብ ውጪ በውሉ መሠረት ይወሰንልኝ በማለት አዲስ ክስ ማቅረብ አይችልም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሽሮ በውሉ መሠረት እንዲፈፀምለት የሚፈልግ ወገን የአፈፃፀም ክስ ማቅረብ ይችላል በማለት መብቱን ጠብቆ መዝገቡን ዘግቶታል። ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

አመልካች በቀን 21/01/2013 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው አቤቱታ በክርክሩ ላይ ያልነበረ ቤቴን እንዳነሳ መወሰኑ ስህተት ስለሆን ይታረምልኝ እያለ ሰበር ሰሚ ችሎቱ አመልካች ያልጠየቀውን ዳኝነት እና ያልተነሳ ክርክርን መሠረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ መሻሩ፤ እንዲሁም ግራ ቀኞችን ያደረገነው የእርቅ ውል ለፍርድ ቤት ቀርቦ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 277 መሠረት ባልፀደቀበት ሁኔታ የአፈፃፀም ክስ እንጂ መደበኛ ክስ አይቀርብበትም በማለት መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን ጠቅሶ ታርሞ እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል።

አቤቱታውም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በግራ ቀኙ መካከል ተደረገ የተባለው የእርቅ ስምምነት በፍርድ ቤት ቀርቦ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 277 እና ተከታይ ድንጋጌዎቹ መሠረት ያልተመዘገበ ስለመሆኑ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገቡን አስቀርቦ ባረጋገጠበት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ በአፈፃፀም የሚታይ ነው በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ የሻረበትን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት በቀን 25/06/2013 ዓ.ም በተፃፈ መልሳቸው አመልካች በአዳኣ በር.ጋ ወረዳ ፍርድ ቤት ያቀረበብኝን ክስ በእርቅ የጨረስን ሲሆን ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነውም ይኸው የእርቅ ውል ነው፤ የወረዳ ፍርድ ቤቱ መዝገብ ጉዳዩ በእርቅ ማለቁን የሚገልጽ ሲሆን የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በእርቅ ማለቁን ግንዛቤ ቢወስድም በመዝገቡ ላይ በምን ጉዳይ እንዳታረቁ አልተገለጸም በሚል ምክንያት ያቀረብኩትን መቃወሚያ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ አልነበረም፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንን በመረዳት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ መሻሩ ተገቢ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍ ባለመሆኑ ሊፀና ይገባዋል በማለት ተከራክረዋል።

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም መዝገቡን ለማስቀረብ የተያዘዉን ጭብጥ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክል ግልባጭ
ፊርማ ቀን 4/10/13
ርዕሰ ጉዳይ
Federal Supreme Court
The Federal Democratic Republic of Ethiopia

ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል። ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለዉ አመልካች ባቀረበዉ ክስ ለጠየቀዉ ዳኝነት መሠረት ያደረገዉ ተጠሪ በአመልካች ይዞታ ላይ የሰራዉን አጥር አፍርሶ ይዞታዉንም ለመልቀቅ በመካከላቸዉ በተደረገዉ የእርቅ ስምምነት የገባዉን ግዴታ አለመፈጸሙን ሲሆን፣ ተጠሪም ይህ የእርቅ ስምምነት በመካከላቸዉ ሰለመደረጉ ክዶ አልተከራከረም። ምንም እንኳ የእርቅ ስምምነቱ የተደረገዉ ይዞታዉን አስመልክቶ በአድአ ወረዳ ፍርድ ቤት ክርክሩ በመታየት ላይ እያለ ቢሆንም የእርቅ ስምምነቱ ለወረዳዉ ፍርድ ቤት ቀርቦ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 277 መሠረት ያልጸደቀ ስለመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገቡን ከወረዳዉ ፍርድ አስቀርቦ ባደረገዉ ማጣሪያ ማረጋገጡን የዉሳኔዉ ይዘት ያስገነዝባል። ዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ከፊለገ በአፈፃፀም ክስ መጠየቅ ይችላል እንጂ ቀጥታ ክስ ማቅረብ አይችልም በማለት ያቀረበዉን መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ ለሰጠዉ ዉሳኔ መሠረት ያደረገዉም የእርቅ ስምምነቱ ከላይ በተመለከተዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ ድንጋጌ መሠረት በፍርድ ቤት አለመጽደቁን ሲሆን፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ አፈፃፀም እንጂ በአዲስ ክስ የሚታይ አይደለም በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰዉ በመካከላቸዉ የተደረገዉ የእርቅ ስምምነት በይግባኝ እስካልተሻረ ድረስ የመጨረሻ ዉሳኔ ነዉ በማለት የፍትሐብሔር ህጉን አንቀጽ 3312(1) ድንጋጌ በዋቢነት በመጥቀስ ስለመሆኑ ከዉሳኔዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል። የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያሻዉ መሠረታዊ ጭብጥም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የእርቅ ስምምነት የዉሳኔ ዉጤት ያለዉ መሆን አለመሆኑ ነዉ።

አለመግባባት በሁለትና ከሁለት በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚፈጠር ነባራዊ ሃቅ መሆኑ ይታወቃል። አለመግባባት በሰዎች የዕርስ በርስ የእለት ተዕለት ግንኙነት መካከል የኖረ፣ ያለ እና የሚኖር ነዉ። የግለሰባዊ ፍላጎት ልዩነት እስካለ ድረስ በሰዎች መካከል አለመግባባቶች መፈጠራቸዉ አይቀሬ ነዉ። በሰዎች መካከል ሊፈጠር የሚችለዉን አለመግባባትን መቀነስ የሚቻል ቢሆንም ማስቀረት ግን አይቻልም። ይልቁንም በዚህ ረገድ መንግስታት ያለባቸዉ ኃላፊነት ወይም ግዴታ ሰዎች በመካከላቸዉ የተፈጠረዉን አለመግባባት በኃይል እና በጉልበት ለመፍታት በሚፈጽሙት ተግባር ምክንያት ግጭቶች እንዳይፈጠሩ ብሎም የዜጎች ፍትሕ የማግኘት መብት እንዲከበር ለማድረግ ይቻል ዘንድ አለመግባባቶች በህግ እና በሥርዓት እልባት የሚያገኙበትን ሥርዓት መዘርጋት ነዉ። አለመግባባቶች በህጋዊ መንገድ መፍትሔ እንዲያገኙ በማድረግ ረገድ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሰዉ ፍርድ ቤት ቢሆንም አለመግባባቶች ከፍርድ ቤት ዉጪ በአማራጭ የሙግት መፍቻ መንገዶች እልባት የሚያገኙበት ሁኔታም በሰፊዉ እየተሰራበት እንደሚገኝ ይታወቃል። አለመግባባቶች ከፍርድ ቤቶች ዉጪ እልባት እንዲያገኙ ማድረግ ያለዉን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች መሠረት በማድረግም ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸዉን ከፍርድ ቤት ዉጪ መፍታት የሚችሉበት ሁኔታ አገራት በህጎቻቸዉ ዕዉቅና ሰጥተዋል። በበርካታ አገሮች በህግ ዕዉቅና የተሰጣቸዉ አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገዶች አራት አይነት ሲሆኑ እነዚህም ድርድር (conciliation)፣ ስምምነት

4/10/13

(negotiation)፣ የግልግል ዳኝነት (arbitration) እና እርቅ (mediation) መሆናቸዉን በዙሪያ የተፃፉ ድርሳናት ያስረዳሉ፡፡

ወደ አገራችንም ስንመጣ ድርድር (negotiation)፣ እርቅ (mediation) እና ግልግል (arbitration) በሀገራችን የፍትሐብሔር ህግ ዕዉቅና የተሰጣቸዉ ሲሆን (በቅደም ተከተል የህጉ አንቀጽ 3307-3317፣ 3318-3324 እና 3325-3348 ይመለከታል)፤ በተለይም ግልግል የሚመራበትን ሥርዓት አስመልክቶ የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉም ሰፊ ድንጋጌዎችን ይዟል (አንቀጽ 315-319፣ 350-357 ይመለከታል)፡፡ የፍትሐብሔር ሕጋችን ምንም እንኳ ድርድር ለሚለዉ ጽንሰ ሃሳብ "ግልግል" የሚል ስያሜ የሰጠዉ ቢሆንም ትርጓሜዉን በአንቀጽ 3307 ስር "ተዋዋይ ወገኖች አንዱ ለአንዱ አንድን ነገር ትቶ ወይም ሰጥቶ የተጀመረዉን ክርክር የሚያቆሙበት ወይም የሚፈጠረዉን ክርክር አስቀድመዉ የሚያስቀሩበት አንድ ዉል" እንደሆነ የገለጸ ከመሆኑ አንፃር ሲታይ ይዘቱ ስለ ግልግል ሳይሆን ስለ ድርድር የሚያሳይ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህም አልፎ ሰዎች አለመግባባታቸዉን ሽማግሌ ተብሎ በሚጠራ ገለልተኛ 3ኛ ወገን በመታገዝ ድርድር በማድረግ በራሣቸዉ ጉዳይ እራሳቸዉ መፍትሄውንና ውጤቱን በመወሰን ሊስማሙ የሚችሉ ሲሆን ይህ በአማርኛዉ እርቅ በእንግሊዝኛዉ mediation በመባል የሚታወቅ ቢሆንም በፍትሐብሔር ህጉ conciliation የሚል ስያሜ የተሰጠዉ ሲሆን ግራ ቀኝ በዚህ ሂደት የሚደርሱበት ስምምነት ዉጤቱ ከድርድር ጋር ተመሳሳይ ነዉ፡፡ ይህም ማለት ግራ ቀኝ በእራሳቸዉ ወይም በሦስተኛ ወገን አማካይነት በሚያደርጉት ድርድር የደረሱበት ስምምነት በሁለቱ መካከል እንደ ፍርድ ተቆጥሮ ተፈፃሚነት ያለዉ ስለመሆኑ ከህጉ አንቀጽ 3312 እና 3324 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሦስተኛዉ ዓይነት ሙግት መፍቻ መንገድ የግልግል ዳኝነት /Arbitration/ በመባል የሚታወቅ ሲሆን ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን የግልግል ዳኛ ተብሎ በሚጠራ ገለልተኛ ሰው እንዲታይላቸው የሚያቀርቡበትና የግልግል ዳኛው በጉዳዩ ላይ ውሣኔ የሚሰጥበት ዘዴ ሲሆን ይህም በህጉ ከአንቀጽ 3325 እና ተከታዮቹ ላይ የተመለከተዉ ነዉ፡፡ የግልግል ዳኝነት መደበኛ የሆነውን ሥነ-ሥርዓት ህግን ተከትሎ ክርክሮችን መምራትን የሚጠይቅ በመሆኑ በባህርዉ ከፍርድ ቤት ሙግት ጋር ይመሳሰላል፡፡ በተጨማሪም ከላይ ከተመለከቱት ሁለቱ አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገዶች በተለየ ሁኔታ በዚህኛዉ የሙግት መፍቻ ዘዴ መሠረት ዉሳኔ የሚሰጠዉ በተከራካሪ ወገኖች ስምምነት መሠረት ሳይሆን በግልግል ዳኛዉ እራሱ መሆኑ እና ዉሳኔዉም ይግባኝ የሚቀርብበት እንዲሁም በቀጥታ በአፈፃፀም በቀጥታ ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ነዉ (የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 3345፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 315-319 እና አንቀጽ 350-357 ይመለከታል)፡፡

ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለዉ ተከራካሪዎች እራሳቸዉ በሚያደርጉት ድርድር ወይም በሦስተኛ ወገን አደራዳሪነት የሚደርሱባቸዉ ስምምነቶች ሁለቱን ተከራካሪ ወገኖች የማስገደድ ዉጤት የሚያስከትል እና ይግባኝ የማይቀርብበት ሲሆን፤ ለግልግል ዳኛ የቀረበ ሲሆን ግን

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
The Federal Supreme Court of The Federal Democratic Republic of Ethiopia
4/10/13

ውሳኔው የሚሰጠው በእራሱ በግልግል ዳኛው ሆኖ በስምምነት የይግባኝ መብት ካልተገደበ በስተቀር ውሳኔውም ይግባኝ የሚቀርብበት እና በቀጥታ ለአፈፃፀም የሚቀርብ መሆኑን ነው። እያንዳንዱ ዓይነት አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ ከሚያስከትለው ህጋዊ ውጤት ጋር በተያያዘ አለመግባባት መፈጠሩን ተከትሎ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም በህጉ የተመለከተው ድንጋጌ ውጤት እንዲኖረው ሊያደርግ የሚችል፣ የህጉን ትክክለኛ ይዘት እና መንፈስ የተከተለ ትርጉም በመስጠት ህጉን ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት እንዳለበት እመነ ነው።

ከዚህ አንፃር የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከት አመልካች ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት ሲታይ በፍርድ ቤት ክርክር ከጀመሩ በኋላ በሽማግሌዎች አማካይነት ስምምነት በማድረግ በመካከላቸው የነበረውን አለመግባባት መፍታት የቻሉ ቢሆንም ተጠሪ በስምምነቱ መሠረት መፈጸም የሚገባውን አልፈጸመም የሚል ይዘት ያለው ነው። ይህም የሚያሳየው ግራ ቀኝ በመካከላቸው የነበረውን አለመግባባት የፈቱበት ዘዴ በባህርው በአንቀጽ 3318 እና ተከታዮቹ ስር የተመለከተው "እርቅ (mediation)" በመባል የሚታወቅ መሆኑን ነው። ከላይ እንደተገለጸው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ክስ የሚቀርብበት አይደለም በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰው የህጉን አንቀጽ 3312 ድንጋጌ በመጥቀስ ነው። በእርግጥ ይህ ድንጋጌ ግልግል በተዋዋይ ወገኖች መካከል ይግባኝ ሳይኖረው የመጨረሻ ፍርድ እንደሆነ እንደሚቆጠር የሚያስቀምጥ ሲሆን የእንግሊዝኛው ቅጂ "As between the parties, the compromise shall have the force of res judicata without appeal" በማለት ይደነግጋል። በህጉ አንቀጽ 3324 መሠረት ይህ ድንጋጌ ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚነት አለው።

በዚህ ድንጋጌ መሠረት ግራ ቀኝ በመካከላቸው ለተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት የሆነውን ጉዳዩ እራሳቸው በሚያደርጉት ድርድር ወይም በሦስተኛ ወገን (ሽማግሌዎች) አማካይነት በሚያደርጉት ስምምነት ከጨረሱ በኋላ ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ በድጋሚ ክስ ማቅረብ አይችሉም። በሌላ አገላለጽ በድንጋጌው በአማርኛ "የመጨረሻ ፍርድ እንደሆነ የሚቆጠር ነው" ወይም በእንግሊዝኛው res judicata ነው በሚል የተገለጸው አገላለጽ ሲታይ ስምምነቱ እንደ ፍርድ ሆኖ ግራ ቀኝን የሚያስገድዳቸው በመሆኑ በስምምነት ወይም በሽምግልና ያለቀ ጉዳይ በድጋሚ እንደ አዲስ ክስ ሆኖ ለፍርድ ቤት ሊቀርብ አይገባም ለማለት እንጂ በስምምነቱ መሠረት ያልተፈጸመ ግዴታ ካለ ይሄው በፍርድ ኃይል እንዲፈጸምለት በስምምነቱ መብት ያገኘ ወገን የሚያቀርበው ክስ ለፍርድ ቤት እንዳይቀርብ የመከላከል ሃሳብ ህጉ የሌለው መሆኑን ነው። ይልቁንም እንደዚህ ዓይነት ስምምነት በፍርድ ቤት እንደተሰጠ ፍርድ የሚቆጠረው እና በቀጥታ በአፈፃፀም ሊቀርብ የሚችለው የእርቅ ስምምነቱ የተደረገው በፍርድ ቤት በሂደት ላይ ላለ ጉዳይ እልባት ለመስጠት የተደረገ ሆኖ ስምምነቱም በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 277 መሠረት ለፍርድ ቤት ቀርቦ የጸደቀ እንደሆነ ነው።

የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከት አመልካች ያቀረበው ክስ በድጋሚ ያቀረበ ነው ለማለት ይቻል የነበረው አመልካች በመካከላቸው የተደረገውን የእርቅ ስምምነት ወደ ጎን በመተው

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
Federal Supreme Court
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
41/10/13

በመካከላቸዉ ለተፈጠረዉ የመጀመሪያዉ አለመግባባት ምክንያት የሆነዉን ጉዳይ የክስ ምክንያት አድርጎ ለፍርድ ቤቱ ያቀረበ ቢሆን ኖሮ ነበር። ይሁንና አመልካች በክስ ምክንያትነት የጠቀሰዉ በመካከላቸዉ የነበረዉ አለመግባባት በእርቅ ስምምነት መቋጫ ያገኘ ቢሆንም ተጠሪ በስምምነቱ መሠረት አለመፈጸሙን እንጂ ከእርቅ ስምምነቱ በፊት የነበረዉን አለመግባባት አይደለም። ይህ ደግሞ አመልካች በተጠሪ ተጥሷል ያለዉ ስምምነት በፍርድ ኃይል እንዲፈጸምለት መጠየቁን የሚያሳይ በመሆኑ በድጋሚ የቀረበ ክስ ነዉ ለማለት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት የለም።

ሲጠቃለልም ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነዉ የእርቅ ስምምነት በባህርዉ በግራ ቀኝ ላይ መብትና ግዴታን የሚጥል፣ ለተፈጠረዉ አለመግባባት እልባት የሰጠ ከመሆኑ አንፃር እንደ ፍርድ ተቆጥሮ በስምምነት ያለቀዉ ጉዳይ በድጋሚ የክስ ምክንያት ሆኖ እንዳይቀርብ የመከላከል ዉጤት ያለዉ ቢሆንም እንደ ፍርድ ተቆጥሮ በቀጥታ የአፈፃፀም ክስ የሚቀርብበት አይደለም፤ ስምምነቱ በቀጥታ ለአፈፃጸም መቅረብ የሚችለዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 277 መሠረት ለፍርድ ቤት ቀርቦ ሲጸድቅ ብቻ ሲሆን ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ አለመጽደቁም ተረጋግጧል። ጉዳዩን ከዚህ አንፃር ማየት ሲገባዉ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች አፈፃፀም ከመጠየቅ ዉጪ አዲስ ክስ ማቅረብ አይችልም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ስምምነት መሠረታዊ ባህርይ እና የፍትሐብሔር ህጉን አንቀጽ 3312 ድንጋጌ ትክክለኛ ይዘት እና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል። ተከታዩም ተወስኗል።

ዉሳኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 320441 በቀን 17/06/2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በአብላጫ ድምጽ የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽሯል።

2. የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተዘግቶ የነበረዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በግራ ቀኝ መካከል በተደረገዉ የእርቅ ስምምነት መሠረት ተጠሪ ኃላፊነት ያለበት መሆን አለመሆኑን አስመልክቶ የመሰለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 341 (1) መሰረት ተመልሶለታል።

3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

ማ/አ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የኦሮሚያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ፍርድ ቤት
The Federal Supreme Court
The Federal Democratic Republic of Ethiopia